የወ/መ/ቁጥር 165535

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 09 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ አባ ወ/ጊዮርጊስ አሸብር - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ታህሳስ 22 ቀን 2002 ዓ.ም በተግፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሌላ ሰው ላይ ፍርሀትን በሚፈጥር ሁኔታ ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 ልዩ ቦታው አቡነ ሀብተማርያም ቤተክርስቲያን ውስጥ ግል ተበዳይ አባ ሳሙኤል ቀለመወርቅን አሳይሀለሁ፤ በእጇ ውስጥ ነው ያለኸው፤ ገና ምኑን አይተህ የጎዳና ተዳዳሪ ነው የማደርግህ ብሎ በማስፈራራቱ በፈፀመው የዛቻ ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀመኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሦስት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ቀርበው እንደመሰከሩትም በክሱ ላይ በተመለከተው ጊዜ፤ ሰዓትና ቦታ ተከሳሽ የግል ተበዳይ አባ ሳሙኤል ቀለመወርቅ የተባሉት የገዳሙ አገልጋይን ቆይ አንተ መለኩሴ የጎዳና ተዳዳሪ አደርግሀለሁ፤ በእጇ ውስጥ ነህ፤ መናፍቅ ነህ ብለው የተናገሯቸው መሆኑን ያስረዱ ሲሆን በዚህም መሰረት ዐ/ሕግ እንደ ክስ አቀራረቡ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ላይ የተደነገገውን የተላለፉ መሆናቸውን ያስረዳ ስለሆነ በተከሰሱበት ድንጋጌ ስር እንዲከላከሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብለው ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም በወቅቱ የዛቻ ድርጊቱን እንዳልፈፀምኩ፤ የዐ/ሕግ ምስክሮች ከግል ተበዳይ ውጭ ቀርበው የመሰከሩት በወቅቱ በቦታው እንዳልነበሩ ያስረዱልኛል ብለው በዚሁ መሰረትም መጋላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ አስተባብለዋል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን በዚህም መሰረት የተከሳሽ ሁለት የመከላከያ ምስክሮች በዕለቱ ከሌሊቱ 9፡ 00 ሰዓት ጀምሮ በቤተክርስቲያኑ እንዳደሩ የገለፁ ቢሆንም ጠዋት 12፡ 00 ሰዓት የቤተክርስቲያን ኪዳን አድራሽ ነን፤ ስርዓቱንም እየፈፀምን ነበር በማለት ከመግለፃቸው አንፃር የግል ተበዳይን ተከሳሽ በክሱ ላይ የተገለፀውን የዛቻ

ድርጊት ሲናገሩ ለመስማት የሚችሉበት ምክንያት ሊኖር እንደማይችል ነው ፍ/ቤቱ ለመገንዘብ የቻለው። ምክንያቱም ኪዳን የሚያደርሱ ዲያቆናት ቃለ እግዚአብሔርን የሚገልፀ በመሆኑና ይህም የሚደረገው በፍፁም ልብ ሀሳብን ወደ እግዚአብሔር በማድረግ በመሆኑ ሌላውን ነገር ማለትም በወቅቱ የግል ተበዳይን ተከሳሽ የተናገሩትን ይሰማሉ የሚባል አይደለም። እንዲሁም እነዚህ የተከሳሽ ሁለት የመከላከያ ምስክሮች ከግል ተበዳይ ውጭ የቀረቡት የዐ/ሕግ ምስክሮች በወቅቱ በቦታው አልነበሩም በማለትም አልመሰከሩም። ከዚህ ሌላ የዐ/ሕግ ምስክሮች በተለይም ገለልተኛ የሆኑት ሁለቱ በማያጠራጥር ሁኔታ አስተዳዳሪያቸውን ሳይፈሩ እውነቱን ተናግረዋል የሚል እምነት ፍ/ቤቱ ስላሳደረ የተከሳሽን የመከላከያ ምስክርነት በዚህ ምክንያት ውድቅ በማድረግ ተከሳሽን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

የቅጣት አስተያየት

ዐ/ሕግ፣ ተከሳሽ በወ/መ/ቁጥር 122153 ጥፋተኛ ተብለውና ተቀጥተው አሁን በገደብ ነው ያሉት፤ በዚሁ ችሎት ነው የተቀጡት፤ ሌላ ደግሞ በወ/መ/ቁጥር 165354 ተከሰው ከግል ተበዳዩ ጋር ታርቀው መዝገቡ የተዘጋ ቢሆንም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 151(2) መሰረት የፍርድ ውጤት ያለው ስለሆነ ይህም የጥፋተኝነት ሪከርድ ስላለው ፍ/ቤቱ ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(ሐ) መሰረት ቅጣቱን በማክበድ እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

ተከሳሽ፣ ዕድሜዬ 40 ዓመት ነው፤ የወር ገቢዬ ብር 1500.00(አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ ዲፕሎማ ሲሆን፤ ቤተሰብ እረዳለሁ፤ የምኖረውም በቤት ኪራይ ነው በማለት አመልክተዋል።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትህዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580/የዛቻ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው ጠዋት ሰዎች ባሉበት በመሆኑና ሌላ የወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙን የሚያከብድ ነገር ፍ/ቤቱ ስላላገኘ የወንጀል ደረጃው ዝቅተኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 580 ለወንጀሉ የተደነገገውን ቅጣት ስንመለከት ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር አምስት መቶ በማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጣ ስለሆነ ተከሳሽን ያርማል ያስተምራል ብሎ ፍ/ቤቱ ያመነው በእስራት መቅጣት ነው ብሎ ስላመነ በዚሁ በእሰራት እንዲቀጡ ተወስኗ።

በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 580 የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከአስር ቀን እስከ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ቀላል እስራት የቅጣት እርዝመት ለአራት ተከፍሎ ስሌቱን በመስራት የተገኘው ውጤት ዝቅተኛ ደረጃ የሚለው የሚወድቀው ከአስር ቀን እስከ 52 ቀን ተኩል ባለው መካከል ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 13(7) መሰረት ሰላሳ ቀን መነሻ ቅጣት ተብሎ ተወስኗል።

ይህ በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት በአባሪ አንድ እርከን 2 ላይ የሚታይ ሲሆን ፍቃደ ስልጣኑም/range/ ከአስር ቀን እስከ ሦስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት አንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን እስራት ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84(1)(ሐ) መሰረት ተከሳሽ ከአሁን በፊት በወንጀል ድርጊት የተቀጣ ስለሆነ ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን በማለት ያመለከተና በማስረጃም የተደገፈ ስለሆነ እርከኑ በአንድ ከፍ ብሎ እርከን 3 እንዲሆን ተደርጓል።

ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርብ ተጠይቆ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 ላይ በተገለፀት መሰረት ያላቀረቡ በመሆኑ እንደ ቅጣት ማቅለያ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 3 ላይ የተመለከተው ፈቃደ ስልጣን/range/ ከሁለት ወር እስከ አምስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን ፍ/ቤቱም ተከሳሽ በሦስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት በተከሳሽ ላይ የተወሰነውን የእስራት ቅጣት ከዛሬ ጀምሮ በማሰብ እንዲያስፈፅም ታዟል።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።